https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23 Year No.13
ADDIS ABABA, 24 January ,2017

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፫፻፺፮/፪ሺ፱ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ…………ገጽ ፱ሺ፭፻፲፩

**CONTENT**

Regulation No. 396/2017
Ethiopian Horticulture and Agricultural Investment Authority Establishment Council of Ministers Regulation ……....page 9511

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፮/፪ሺ፱

## የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና ፴፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፮/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "ሆርቲካልቸር" ማለት አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ አበባ እና እፀጣዕም ሰብሎችን ልማትና ግብይት የሚያጠቃልል የተግባር ሂደት ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 396/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN HORITICULTURE AND AGRICUTURAL INVESTMENT AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to the Article 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Horticulture and Agricultural Investment Authority Establishment Council of Ministers Regulation No. 396/2017".

### 2. Definitions

In this Regulation:

1/ "horticulture" means activity that includes production and marketing of vegetables, fruits, floriculture and herbs;

https://chilot.me



፪/ "የምግብ ደህንነት መሥፈርቶች" ማለት የአትክልትና ፍራፍሬ እና ሌሎች የምግብ ሰብሎች ምርት ለሰዎች ጤና ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የወጡ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያጠቃልላል፤

፫/ "ኮሜርሻል ግብርና ኢንቨስትመንት" ማለት በሰብል፣ በእንስሳት እና በደን ዘርፍ አዳዲስ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንትን ለማቋቋም ወይም ነባር የግብርና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

፬/ "የግብርና ኢንቨስትመንት ሥነ-ምግባር መሥፈርት" ማለት የግብርና ኢንቨስትመንት የአካባቢንና የማህበረሰብ ደህንነትን እንዲሁም ዘላቂ ልማትን በጠበቀ መልኩ የምርት ሂደቱ መካሄዱንና ምርቶች ለሰዎች ጤና ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የወጡ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያጠቃልላል፤

፭/ "የግብርና ኢንቨስትመንት ዞን" ማለት ለባለሀብቶች የግብርና ሥራ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ከክልሎች ጋር በመተባበር የተስካለለ እና አስፈላጊ መሠረተ ልማት አውታሮች የተሟሉለት የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት ወይም አካባቢ ነው፤

፮/ "የመሬት ባንክ" ማለት ባለሥልጣኑ ከክልሎች ተረክቦ የሚያስተዳድራቸውን መሬቶች መዝግቦ የሚይዝበት የመሬት መረጃ ሥርዓት ነው፤

፯/ "ሆርቲካልቸር ኮሪደር" ማለት በአገሪቱ በተለያዩ ክልሎች የሆርቲካልቸር ሰብሎች የሚመረቱበት ወይም ሊመረቱ የሚችሉ ተስማሚ ሥነ-ምህዳር ያለው አካባቢ ነው፤

2/ "food safety standards" includes domestic and international standards enacted to ensure the safety of vegetables, fruits and other crops for human health consumption;

3/ "commercial agriculture investment" means a capital investment of an investor to establish a new large agricultural investment farms, ranches and commercial plantation forest or for expansion or improvement of existing agriculture investment farms;

4/ "agriculture investment code of practice" includes national and international code of practices enacted to ensuring that the production of agricultural investment activities are friendly with the environment, community safety and sustainable development; and the products are suitable for human health;

5/ "agriculture investment zone" means agricultural farm land or area delineated for agricultural investment in collaboration with Regional States and for which necessary infrastructures and facilities are fulfilled to creating conducive working environment for the investors;

6/ "land bank'' means a data base system where the authority registers and administers those lands transferred from regions;

7/ "horticulture corridor" means a suitable agro-ecology area of various Regional States where horticulture crops are commonly produced or suitable potential for the development of the same;

https://chilot.me



፰/ “አውትግሮወርስ” ማለት በሆርቲካልቸርም ሆነ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማራ ባለሀብት ወይም ድርጅት እና ግለሰብ አርሶ አደር ወይም ቡድን ወይም ማህበራት ሕጋዊ ውል በመዋዋል ከማሳ ዝግጅት እስከ ምርት አሰባሰብ ድረስ ባለው ሂደት የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል የሚደረግበትና በውሉ በተመለከተው መሠረት ጥራት ያለው ሰብል የሚመረትበት፣ ክፍያ በወቅቱ ለአርሶ አደሮች የሚፈጸምበት እና ውል ለተገባው ባለሀብት ወይም ድርጅት ብቻ የምርት ርክክብ የሚፈጸምበት አሰራር ሂደት ነው፤

፱/ “ኮንትራት እርሻ” ማለት በሆርቲካልቸርም ሆነ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማራ ባለሀብት ወይም ድርጅት ከግለሰብ አርሶ አደር ወይም ከማህበራት ጋር ሕጋዊ ውል በመዋዋል በውል የተመለከተውን የግብርና ምርት ወይም የተቀነባበረ የግብርና ምርቶችን በግዥ በመረከብ ለተሻለ የጋራ ጥቅም በሚደረግ ስምምነት የሚካሄድ እርሻ ልማት ነው፤

፲/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፩/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፪. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ “ባለሥልጣን” እየተባለ

8/ “out growers” means an agreement based production arrangement with farmer or group of farmers or farmers’ associations who are entered into agreement with an investor or investment company where technical and follow up support are provided from field preparation to product harvest and as per the agreement the quality of crop production is maintained, timely payment is effected to farmers and the yield of which shall only be handed over to the investor;

9/ “contract farming” means an agreement based production arrangement between horticulture or agricultural investor and an individual farmer or farmers’ associations to receive agricultural product or value added products through purchase in accordance with the agreement signed and endorsed by both parties for mutual benefit;

10/ “Region” means any Regional State referred to under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa city administration and Dire Dawa administration;

11/ “person” means any natural person or juridical body;

12/ any expression in the masculine gender includes the feminine;

## 2. Establishment

1/ There is established the Ethiopian Horticulture and Agricultural Investment Authority (in this Regulation referred as the “Authority”) as autonomous federal

https://chilot.me



የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተ፯ ፱ሺ፭፻፲፩

፪/ የባለሥልጣኑ ተጠሪነት በመንግስት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፬. **<u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **<u>ዓላማ</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

፩/ ከክልሎች ጋር በመተባበር ለሆርቲካልቸርና ለገበያ ለሚቀርቡ የግብርና ምርቶች የሚውሉ ኢንቨስትመንት መሬቶችን በጥናት በመለየት፤ አቅርቦቱን ማመቻቸት እና ዝርዝር የሰብል፣ የእንስሳትና የደን ልማት ተስማሚነት ሰነድ በማዘጋጀት አቅም ላላቸው ባለሀብቶች እንዲተላለፍ መደገፍ፤

፪/ ለባለሀብቱ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት ለሆርቲካልቸርና ለግብርና ኢንቨስትመንት የተላለፈ ውን መሬት ሙሉ በሙሉ ወደ ልማት እንዲገባ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብዓት እና የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርት አቅርቦትን ማሳደግ፤

፫/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ቀልጣፋና የተቀናጀ የሎጂስቲክስ አገልግሎትን በመዘርጋት እና አማራጭ ገበያን በማስፋት የሆርቲካልቸር ምርቶችን ኤክስፖርት፣ የግብርና የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦትንና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፡፡

፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት

government organ having its own legal personality.

2/ The Authority's accountability shall be determined by the Government.

4. **<u>Head Office</u>**

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. **<u>Objective</u>**

The Authority shall have the following main objectives:

1/ in collaboration with regional states study and identify agricultural investment lands suitable for the production of horticulture, commercial farms, livestocks and commercial plantation forest facilitate supply of investment land and provide suitability documents, make those documents accessible to the users/investors and support transfer of land;

2/ provide comprehensive supports to agricultural investors and ensure maximum utilization of investment land transferred and enhance production and productivity to strengthen adequate supply raw materials to the industry and enhance foreign earnings from horticulture products;

3/ In collaboration with the relevant bodies; facilitate and integrate logistic services and alternative new market destinations and encourage horticulture export, supply of raw material demand for agro-industries and growth foreign Currency .

6. **<u>Power and Duties</u>**

The Authority shall have the following powers and duties:

1/ prepare, as may be necessary by engaging stakeholders policies, strategies and laws which support large scale commercial farming investment that ensures fast and

https://chilot.me



ይኖሩታል፡፡

፩/ የሆርቲካልቸርና ለገበያ የሚያመርቱ ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ሥራዎችን ዕድገት ፍጥነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥና መልካም ተሞክሮዎችን ለመቀመር የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን እንዳስፈላጊነቱ ፱ሺ፭፻፲፭ ቹውን ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዮችን በማሳተፍ ያዘጋጃል፣ ለመንግስት ቀርቦ ይሁንታ ሲያገኝና ሲፈቀድም ትግበራውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/ የሆርቲካልቸርና ሰፋፊ ኮሜርሻል ግብርና ልማትንና ግብይትን በቀጣይነት ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዱ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ መርሃ ግብሮችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡

፫/ ከክልሎች እና አግባብ ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር የሆርቲካልቸርና የሰፋፊ ኮሜርሻል ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት በጥናት ይለያል፣ ከሦስተኛ ወገን ይዞታ ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል፣ የሰብልን፣ የእንስሳትንና የደን ልማትን ተስማሚነት ዝርዝር ጥናት በማካሄድ የመሬት መረጃ ፕሮፋይል ያዘጋጃል፣ የመሬት ባንክ ሥርዓት ያደራጃል፣ የመረጃ ቋት እንዲደራጅ ማድረግና የሥነ-ምህዳር፣ የአፈር ቶፖግራፊ፣ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሀ፣ የጂኦግራፊና የሶሽዮ ኢኮኖሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ ያደራጃል፡፡

፬/ ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተዘጋጀው መሬት የሰብልን፣ እንስሳትንና የደን ልማትን ተስማሚነት ሰነድ ያዘጋጃል፣ በተለያዩ ዘዴዎች ለባለሀብት ያስተዋውቃል፣ ባለሀብቶችን በመመልመል መሬት እንዲተላለፍ ይደግፋል፡፡ በውክልና የተሰጡ መሬቶችን በቀጥታ ያስተላልፋል፡፡ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

sustainable growth of horticulture and for benchmarking of best experiences and submit to the Government; upon approval by the Government follow up and monitor the implementation of same;

2/ prepares short, medium and long term plans so as to expand and foster horticulture and large scale commercial farming investment and upon approval follow up the implementation;

3/ in collaboration with regional states and other bodies identify and verify horticulture and commercial agricultural investment lands, make sure land is free from third party possession; conduct crop, live stocks and forest suitability studies and prepare soil information data, develop a land bank system and collect and compile basic data on soil, agro-ecology, topography, ground and surface water sources and socio-economy;

4/ in collaboration with regional states and other stakeholders prepare crop, live stocks and forest suitability document for agricultural investment land made ready; promote the land using different medias, support regions in recruitment of investors and transfer of lands, transfer lands under its land bank, and follow up its implementation;

5/ in collaboration with relevant regional states and other stakeholders conduct study and organize horticulture development corridors and agricultural investment zones and create conducive investment environment;

https://chilot.me



፮/ ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሆርቲካልቸር የልማት ኮሪደርና የግብርና ኢንቨስትመንት ዞን በማጥናትና በማደራጀት ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፯/ ከተመረጡ ምርምርና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና አግባብነት ካላቸዉ ሌሎች ባለድርሻዎች ጋር ፱ሺ፰፻፲ [illegible] የዘርፉን አቅም በዕውቀትና በክህሎት ለመገንባት በጋራ ይሰራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፰/ ከተመረጡ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሆርቲካልቸር እና የግብርና ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲስፋፉ ድጋፍ ይሰጣል፤ ከአምራቾችና ከላኪዎች ጋር በአጋርነት ይሠራል፣ በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶች እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፱/ በዘርፉ እሴት ሰንሰለት የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የጥናት ውጤቶች ሥራ ላይ የሚውሉበትን ስልቶችና አሠራሮችን ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲/ በሆርቲካልቸርና በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በአውትግሮወርስና ኮንትራት እርሻ አሰራር ከአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር እንዲተሳሰሩ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፩/ ለሆርቲካልቸርና ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚያስፈ ልጉ መሠረተ ልማቶች፣ የምርት ማሳደጊያ ግብአቶች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ ማሸጊያዎች እና ሎጂስቲክስ አቅርቦቶች በወቅቱ በተፈለገው መጠንና ጥራት እንዲሁም በተወዳዳሪ

6/ in cooperation with specific research and higher education institutions and other stakeholders work with others to build the capacity of the sector in knowledge and skills, follow up its effective implementation;

7/ in collaboration with specific institutions conduct benchmark local and foreign best practices and improved technologies of horticulture and agricultural investment; promote and support its implementation; work in cooperation with producers and exporters to participate in international exhibition and trade fairs;

8/ conduct studies on challenges in supply chain of the sector and develop appropriate strategies to resolve constraints prevailing and follow up its implementation;

9/ facilitate, provide integrated support and follow up out grower scheme and contract farming systems to engage farmers and investors in horticulture and large scale commercial farming investment;

10/ follow up adequate supply and required quality pre- and post harvest technologies and services like infrastructure, inputs, farm machineries, packing materials and logistics to investors with competitive price; in coordination with relevant bodies, follow up and monitor that the investment incentives are used for the intended purposes;

11/ in coordination with regional states and relevant bodies, monitor and evaluate agricultural investment land utilization whether it is in accordance with project plan and land lease agreement and provide expertise advise and

https://chilot.me



ዋጋ የሚቀርብበትን አሠራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤ የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ዎች ለተፈቀደ ላቸው ዓላማዎች መዋላቸውን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፩/ ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት የኢንቨስትመንት መሬቶች አጠቃቀም እና ቢዝነስ ፕላን አተገባበር በተገባው የሊዝ ውል መሠረት ስለመሆኑ ክትትልና የሙያ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሲሆን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያስደርጋል፤
፱ሺ፭፻፲

፲፪/ ከክልሎች እና ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በዘርፉ ሀገራዊ ልማታዊ ባለሀብቶች እንዲፈጠሩ፣ ወጣቶችና ባለሙያዎች በፍላጎት እንዲደራጁ በኢንተርፕሪነርሽፕ በማሰልጠን፣ የመሬት አቅርቦ ትና ብድር የማመቻቸት ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫/ የሆርቲካልቸርና የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማህበራዊና የአካባቢ ጥበቃ ማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የሥነ-ምግባር መስፈርትን ያስተዋውቃል፣ የሆርቲካል ቸር ምርቶች እና የምግብ ደህንነትና ጥራት ደረጃዎችን አፈፃፀም በመከታተል ይደግፋል፤

፲፬/ የግብርና ምርቶች በተለይም የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪነ ታቸውን ለማረጋገጥ ስለተሻለ አመራረት፣ ምርት እንክብካቤ፣ ጥራትና የምግብ ደህንነት ስልጠና እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብት የቴክኖሎጂና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችንና ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፤

technical support and cause corrective measures to be taken whenever necessary;

12/ in collaboration with regional states and relevant bodies, encourage creation of domestic private sector, youths and experts associations based on their interest and provide entrepreneurship trainings, facilitate agricultural investment land provision and loan to the same;

13/ enforce preparation and implementation of plan for social environmental protection in the project areas of horticulture and agricultural investment; promote environmental code of practices and food safety and quality standards in horticulture and agriculture investment sector;

14/ ensure competiveness of agriculture products mainly horticulture export commodities through continuous and intensive capacity building and advisory service on improved farm management; quality standards, food safety issues and product handling; and also develop and implement local investors technology and extension packages and manuals;

15/ organize, manage, follow up and ensure effectiveness of horticulture and agricultural investors consultation forum with stakeholders to provide better support in the sector and implementation of joint decision makings;

16/ collect, analyze and avail domestic and international market and other relevant trends on horticulture and agricultural investment; and follow up its implementation;

17/ own properties, enter into contacts, sue and be sued in its own name;

https://chilot.me



፲፭/ በሆርቲካልቸር እና በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶችና ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ የምክክር መድረክ(ፎረም) በማቋቋም በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ ድጋፎችን ይሰጣል፣ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፲፮/ የሆርቲካልቸርና የግብርና ኢንቨስትመንት ልማትና ግብይት ወቅታዊ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የምርትና ግብይት እንዲሁም ተያያዥ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ በየወቅቱም ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤

፲፯/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፡ ይከሰሳል፤

፲፰/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅና ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፱ሺ፭፻፲፰

**፯. የባለሥልጣኑ አቋም**

ባለስልጣኑ፡-

፩/ በመንግስት የሚሾሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች እና

፪/ አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፰. የዋና ሥራ አስፈጻሚው ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት

18/ perform other relevant activities necessary for the attainment of its objectives.

**7. Organization of the Authority**

The Authority shall have:

1/ A Chief Executive Officer and as may be necessary, Deputy Chief Executive Officers to be appointed by the Government; and

2/ the necessary staff.

**8. Powers and Duties of the Chief Executive Officer**

1/ The Chief Executive Officer shall be the chief executive officer of the Authority and lead and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) this Article, the Chief Executive Officer shall :

a) exercise the powers and duties of the Authority provided under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Authority in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Authority, in accordance with directives approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the government the strategic plan, annual plan and work program and budget of the Authority, and implement same upon approval by government;

d) represent the Authority in all its dealings with third parties.

3/ The Chief Executive Officer may delegate part of his powers and duties to other officials and staff of the

https://chilot.me



እንዲሁም የባለሥልጣኑን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን ስትራቴጂክ እቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፣ በመንግስት ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ባለሥልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፡፡

፫/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፱ሺ.፭፻፲

## ፱. የምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፤

፩/ የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚውን ያግዛሉ፤

፪/ በዋና ሥራ አስፈጻሚው ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናሉ፤

፫/ ዋና ስራ አስፈጻሚው በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና ሲሰጥ ዋና ሥራ አስፈጻሚውን ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፲. በጀት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

## ፲፩. ስለሂሳብ መዛግብት

፩. ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

## 9. Powers and Duties of Deputy Chief Executive Officers

Deputy Chief Executive Officers shall have the following powers and duties:

1/ assist the Chief Executive Officer in planning, organizing, leading and administering the powers and duties of the Authority;

2/ undertake specific assignments entrusted to them by the Chief Executive Officer;

3/ when specifically delegated, act on behalf of the Chief Executive Officer in his absence.

## 10. Budget

The Authority's budget shall be allocated by the Government.

## 11. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by auditors assigned by the Auditor General.

## 12. Repealed and Inapplicable Laws

The Ethiopian Horticulture Development Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 152/2000 and the Ethiopia Agriculture Investment Land Administration Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 283/2005 are hereby repealed.

## 13. Transfer of Rights and Duties

The rights and duties of the Ethiopian Horticulture Development Agency Established under Council of Ministers Regulation No. 152/2000 and the Ethiopia

https://chilot.me



፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረ መራሉ፡፡

፲፪. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፪/፪ሺ እንዲሁም የኢትዮጵያ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፫/፪ሺ፭ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

፲፫. <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፪/፪ሺ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፫/፪ሺ፭ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ የግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባለሥልጣኑ ፱ሺ፭፻፳ [illegible]፡፡

፲፬ <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

Agriculture Investment Land Administration Agency Established under Council of Ministers Regulation No. 283/2005 are hereby transferred to the Authority.

14. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 24th day of January, 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**